# ለሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ ለሒሣብ እና ለኦዲት ባለሙያዎች እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ

የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 መሠረት በርካታ ሥልጣን እና ተግባራት የተሰጠው ሲሆን ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት በማውጣት ይመዘግባል፡፡ በዚሁ መሠረት ቦርዱ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን ከተሰማሩበት የሥራ ዓይነት ወይም ባህርይ፣ የኃብት መጠን ወይም የሠራተኛውን ብዛት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተለውን መስፈርት አውጥቷል፡፡

1. <u>የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት</u> (Public Interest Entities-PIE)

ሀ) <u>ከተሰማሩበት የሥራ ዓይነት ወይም ባህርይ አኳያ</u> የሚከተሉት ድርጅቶች የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት ናቸው፡፡

- የሚያወጡትን የግዴታ ምሥክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለግብይት ያዋለ ወይም ለማዋል በዝግጅት ላይ ያለ ማንኛውም ኩባንያ፤
- ባንኮች፣ የመድን ሰጪ ተቋማት፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያዎች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፤
- በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ የልማት ድርጅት፤
- በሚመለከተው የመንግሥት አካል ቁጥጥር የሚደረግበት የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ የሚያስተዳድር እና ተመሳሳይ ተግባር የሚፈጽም ተቋም፤
- የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት እና በጎ አድራጎት ማኅበራት፤

ለ) <u>ከኃብት መጠን እና ከሠራተኛ ብዛት አኳያ</u> ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል ቢያንስ ሁለቱን ያሟላ ድርጅት የሕዝብ ጥቅም ያለበት ሪፖርት አቅራቢ አካል ነው፡፡

- ዓመታዊ ገቢው ብር 300,000,000.00 (ሦስት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤
- ጠቅላላ ኃብቱ ብር 200,000,000.00 (ሁለት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ

የሆነ፤

- ጠቅላላ ዕዳው ብር 200,000,000.00 (ሁለት መቶ ሚሊዮን) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤ ወይም
- የሠራተኞቹ ብዛት 200 (ሁለት መቶ) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፡፡

** *ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መስፈርቶች ውስጥ የሚመደቡ ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሒሣብ መግለጫቸውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (International Financial Reporting Standards-IFRS) መሠረት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡*

** *የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሒሣብ መግለጫቸውን በዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሒሣብ አያያዝ ደረጃዎች (International Public Sector Accounting Standards-IPSAS) መሠረት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡*

2. <u>አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች (Small and Medium Enterprises-SMEs)</u>

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች መካከል ቢያንስ ሁለቱን የሚያሟላ ድርጅት አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅት ሲሆን የሒሳብ መግለጫውን በአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (International Financial Reporting Standards for Small and Medium Enterprises-IFRS for SMEs) መሠረት ማዘጋጀት አለበት፡፡

- ዓመታዊ ገቢው ብር 50,000,000.00 (አምሳ ሚሊዮን) እና ከብር 300,000,000.00 (ሦስት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤
- ጠቅላላ ኃብቱ ብር 50,000,000.00 (አምሳ ሚሊዮን) እና ከብር 200,000,000.00 (ሁለት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤
- ጠቅላላ ዕዳው ብር 50,000,000.00 (አምሳ ሚሊዮን) እና ከብር 200,000,000.00 (ሁለት መቶ ሚሊዮን) በታች የሆነ፤ ወይም
- የሠራተኞቹ ብዛት 50 (አምሳ) እና ከ200 (ሁለት መቶ) በታች የሆነ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ AABE

3. <u>ጥቃቅን ድርጅቶች</u>

ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ከተመደቡት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ውጪ የሚገኙ ማናቸውም የአክስዮን ማኅበራት፣ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች፣ ቁጥጥር የሚደረግበት የሸማቾች ማኅበር፣ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ አባላት፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ የሽርክና ማኅበር ወይም የግል ድርጅት እንደ ጥቃቅን ድርጅት የሚቆጠር ሲሆን *<u>በፈቃደኝነት</u>* የሒሣብ መግለጫውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡

4. <u>የሪፖርት አቅራቢ አካላት ግዴታዎች</u>

ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ሥር የሚመደቡ የሪፖርት አቅራቢ አካላት ኦዲት የተደረገ የሒሳብ መግለጫቸውን የድርጅቱ የሒሣብ ዓመት በተጠናቀቀ በ 4 (አራት) ወራት ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

በሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 804/2013 መሠረት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሪፖርቱን ያላቀረበ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ድርጅቱ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) እንዲሁም የድርጅቱ ዳይሬክተር/ሥራ አስኪያጅ ብር 100.00 (አንድ መቶ) የገንዘብ ቅጣት እንደሚከፍሉ ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም የፋይናንስ ሪፖርታቸውን በቅጣት ከሚያቀርቡበት የጊዜ ገደብ በኋላ ወደ ቦርዱ የሚቀርቡ ሪፖርት አቅራቢ አካላት በአዋጅ ቁጥር 847/2006 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም የሚመለከታችሁ አካላት ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ተግባራዊ እንድታደርጉ ለማስታወስ እንወዳለን፡፡